# ወይ ፍንክች!

ባልዋልኩበት ውሏል፣ ብለው ቢከሱኝም

ያለህግ - ያለፍርድ ቢወነጅሉኝም፤

ወህኒ-ቤት - ከርቸሌ፣ ቢያወርዱኝ ዘብጥያ

ቢገርፉ - ቢወግሩኝ፣ ከምሽት እስከ አጥቢያ፤

እኔ እንደሁ ወይ ፍንክች! የመጣው ቢመጣ

ከበጎ አላማዬ፣ ከእውነቱ ላልወጣ።

ከሰው ንብረት አልፈው፣ ደም የሚጠማቸው

አሳር ቢያሳዩኝም፣ በእኩይ ምግባራቸው፤

የህይወት ጉዞዬን፣ ቢያደርጉት መራራ

በላዩ ቢከመር፣ ሀዘን ከመከራ፤

በድን አያደርጉት፣ ቆራጥ ህሊናዬን

አያቆሽሹትም ንፁህ - ብሩህ ልቤን።

ሰብአዊነት.... ጠፍቶ ከውስጣቸው

ቢያሳክራቸው የስልጣን ጥማቸው፤

ምንም ምን ቢያደርጉኝ፣ ምንም ምን ብሆን

ወይ ፍንክች! ወይ ፍንክች!.... አልሰጥም እጄን።

ተስፋና ምኞቴን፣ ከግብ ሳላደርስ

የሚያግደኝ የለም አፈር እስከለብስ።

-----//-----

ፊልጶስ / hol-land@hotmail.com

EthioLion.Com